# ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

ሚያዚያ 1 ቀን 2000 ዓ. ም. (April 9, 2008)

የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ኢትዮጵያ ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ያለው ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬት ለሱዳን ለማስረከብ በኢሕአዴግና በሱዳን መንግሥታት መካከል የተደረገን ድብቅ ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ኢሕአዴግ እንቅስቃሴ ጀምሯል። ከመሬቱ እየተፈናቀለ ያለው አርሶ አደር ወገናችን ለከፍተኛ አመፅ እየተነሣሳ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የኢሕአዴግ መንግሥት መሬቱን ለሱዳን ለማስረከብና የአካባቢውን ተቃውሞ በኃይል ለመደምሰስ በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ይገኛል።

የሚቀጥሉት መረጃዎች ጉዳዩ የት እንዳለና ወደ የት ሊያመራ እንደሚችል ይገልጻሉ፤

1ኛ የካቲት 2 እና 3 ቀን 2000 ዓ. ም. (February 10-11, 2008) የኢሕአዴግና የሱዳን ጥምር መልዕክተኛ ቡድን ታች አርማጭሆ ውስጥ ደለሎ በተባለው ቦታ በሌሊት ተገናኝተው አዲሱን የድንበር መለያ ምልክት ሲተክሉ ያየ አንድ የአካባቢው ገበሬ ተኩስ ከፍቶባቸው ቡድኑ በመደናገጥ ወደ ሱዳን እንዲሸሹ ካደረገ በኋላ አብርሃ ጅራና አብደራፊ ወደ ተባሉ ከተሞች ሒዶ ለሕዝብ ጉዳዩን አሰማ። የሁለቱ ከተሞችና የአካባቢው የገጠር ኑዋሪ ሕዝብ በቁጣ በመነሣሳት ወደተባለው ድንበር በመሔድ የተተከለውን የድንበር ምልክት ነቅሎና አፈራርሶ ተመለሰ። የአካባቢው አስተዳደር ተወካይ ሕዝቡን ቀርቦ "ነገሩን በውይይትና በሽምግልና እንጨርሰዋለን" ብሎ ለማግባባት ቢሞክርም ሕዝቡ "በመሬታችንና በርስታችን ሽምግልና አንገባም" በማለት አስተዳዳሪውን መለሰ።

2ኛ መጋቢት 5 ቀን 2000 ዓ. ም. (March 14, 2008) ሳንጃ በተባለው ከተማ የታችና የላይ አርማጭሆ ሕዝብን የጎንደር አስተዳደር ተጠሪ ስብሰባ ጠርቶ "የድንበሩን ክልል በሽምግልናና በውይይት ለመፍታት መንግሥት ዝግጁ ነው" የሚል ሃሳብ ሲሠነዝር "እኛ በርስታችንና በመሬታችን ሽምግልና አንገባም፤ ይልቁንም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ አዲሱ ለገሠ ይምጡና ያነጋግሩን" በማለት ሕዝቡ ስብሰባውን ረግጦ ወጥቷል።

3ኛ ከመጋቢት 6 ቀን 2000 ዓ. ም. (March 15, 2008) ጀምሮ የኢሕአዴግ መንግሥት ድንበሩን ለሱዳን ለማስረከብ ሲል የሕዝቡን ተቃውሞ ለመስበር የአግአዚ ጦሩን በሑመራ አብደራፊ አካባቢ እንዲሁም በመተማ አቅራቢያ ሽንፋ በተባለ ቦታ ከማስፈሩም በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ካድሬዎች ከሑመራ እስከ ቋራ ባሉት ቦታዎች በማሰማራት ሕዝቡ የድንበሩን ውሳኔ በግዴታ መቀበል እንዳለበት፤ አለበለዚያ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያስከትል ማስጠንቀቂያ በማስተላለፍ ላይ ይገኛል። ሕዝቡም "እኛ ለርስታችንና ለአገራችን ድንበር እንታገላለን፤ በዚህ ምክንያት ከሱዳንም ሆነ ከራሳችን መንግሥት የሚደርስብንን ጭፍጨፋና ድብደባ እንቀበላለን እንጂ መሬታችን ሲወሰድ ዝም ብለን አናይም" በማለት የኢሕአዴግ መንግሥት የከዳውን፤ ግን አባቶቻችን የተዋደቁለትን የኢትዮጵያ ጀግኖች አርማ አንግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

በዚህ አሁን በተጋጋለው የሕዝብና የመንግሥት ፍጥጫና ሊከሰት ለሚችለው የደም መፋሰስም ሆነ የንብረት ጥፋት ዋናው ተጠያቂ የኢሕአዴግ መንግሥትና በየደረጃው የተሳተፉ ባለሥልጣናት መሆናቸውን ከወዲሁ ልናስገነዝብ እንወዳለን።

የዚህን የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ በተመለከተ ወደፊት በዝርዝርና በመረጃ የተደገፈ ጥናታዊ ጽሑፍ የምናቀርብ ሲሆን ለአሁኑ በአጭሩ ከታች የተጠቀሱት ማስረጃዎች የድንበሩን ታሪካዊ ሁኔታ ይገልጻሉ።

1ኛ ድንበሩ በኢትዮጵያና እንግሊዝ ወይም በኢትዮጵያና ሱዳን መንግሥታት ወኪሎች ተረጋግጦ የተከለለ ሳይሆን ጉዊን በተባለ አንድ የእንግሊዝ ሻለቃ የተሠመረ፣ ፊርማ የሌለበት ካርታ ነው በሱዳን በኩል እንደ መረጃ የሚቀርበው።

2ኛ ይህ ክልል  በዚህ ሰው ካለምንም ተጨባጭ ማስረጃ ከመሠመሩ በፊትም ሆነ በኋላ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪሎች ግብር የሚያስከፍሉበትና የሚያስተዳድሩት ክልል ነው።

3ኛ በደርግ ዘመን በመንግሥት የተመረጡ አምስት ምሑራን ያሉበት ቡድን  የኢትዮጵያ የግዛት ክልል የሱዳን መንግሥት የሚለው ሳይሆን፤ ይልቁንም ኢትዮጵያ ከሱዳን የምትፈልገው ሰፊ መሬት እንዳለ  በሰፊው አጥንቶ ሪፖርት አቅርቦ ጥያቄውን ለአንዴና ለመጨረሻ ዘግቶት ነበር።

አሁን ያለውን አጋጣሚ በመጠቀም ይህ ለምና ሰፊ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን አንዳንድ የዜና አውታሮች በተለይም ሱዳን ትሪቢዩን ጋዜጣ በሰፊው መዘገባቸውን የተከታተልን በሰሜን አሜሪካ የምንኖር ኢትዮጵዊያን "የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ" አቋቁመን፤ በመጀመሪያ ነሐሴ 2 ቀን 1999 ዓ. ም. (August 8, 2007) በአማርኛና በእንግሊዘኛ በተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በጉዳዩ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ እንዲሰጡበትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ እንዲያደርጉ ጠየቅን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስካሁን የሰጡት መልስ የለም። ከዚያም በማከታተል ጥር 10 ቀን 2000 ዓ. ም. (January 19, 2008) በተለያዩ ድኅረ ገጾች ላይ ባሰራጨነው ጽሑፍ፡-

ሀ. ድንበሩን አስመልክቶ አቶ መለስ ዜናዊ ከሱዳን ባለሥልጣናት ጋር ካርቱም መገናኘታቸውና የሁለቱ መንግሥታት ተወካዮች ደግሞ በተባለው ድንበር ደጋግመው መገናኘታቸውን፤

ለ. የተሰጠው የድንበር መሬት ከጋንቤላ እስከ ሑመራ እንደሚደርስ ከሱዳን የዜና አውታሮች ያገኘነውን ልዩ ልዩ መረጃ ለመላ አገር ወዳድ አቀረብን። አያይዝንም የበለጠ መረጃ በማሰባሰብ ላይ መሆናችንና በጥናታዊ ጽሑፍ የተደገፈ አቤቱታ ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሰማት በዝግጅት ላይ መሆናችንን ገልፀን በዚሁ ጉዳይ ላይ መረጃዎች ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ሁሉ እንዲተባበሩን ጥሪ አቅርበናል።

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ማኅበራት፣ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች በታሪክ የሱዳን ሆኖ የማያውቀው፣ ሕዝቡ እየተዋደቀ ያቆየው፣ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውን የኢትዮጵያ አንጡራ ለም መሬት (ርስት) በከንቱ አሳልፎ እንዳይሰጥ በኢሕአዴግ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዲያደርግ፤ የሱዳንም መንግሥት የማይገባውን የሕዝብ መሬት ለመውሰድ የሚያደርገውን ግፊት እንዲያቆም ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ እንዲያስተላልፍልን፤ በዚህ ጉዳይ በምናደርገው እንቅስቃሴም ትብብር እንዲያደርግልን በትግል ላይ በሚገኘው ወገናችን ስም እናሳስባለን።

የድንበሩ ጉዳይ ኮሚቴ ይህን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ በቅርብ በመከታተል ላይ ሲሆን፤ የሁኔታውን ዕድገት በተመለከተ ተከታታይ መግለጫዎችን የሚያወጣ መሆኑን እንገልጻለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በልጆቿ ይከበራል!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ